በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፩


መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሐምሌ ፪ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.**

# መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፩

- ይህ ርዕስ በዓለም ውስጥ ለምንኖር የሚያስፈራ እንጂ የሚያስደስት ርዕስ ላይሆን  ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ልንረዳው የሚገባ በጣም አስፈላጊ ርዕስ ነው፤ በዓለም ስንኖር እንፈተናለን መንፈሳዊ ጦርነትም አለና፡፡
- በክረምት ከጭቃ፣ ከብርድ… በላይ ሊያሳስበን የሚገባ ጉዳይ አለ እርሱም መንፈሳዊ ውጊያ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች እንደዚህ ያለ ነገር የለም ብለው ራሳቸውን አሳምነዋል፣ ሌሎች ደግሞ ዲያቢሎስንና ውጊያውን ሲያስቡ ይጨነቃሉ ወይም ይፈራሉ፡፡
- መንፈሳዊ ውጊያ ስንል አስማት፣ ጥንቆላ፣ … አይደለም፡፡ ብናምንም ባናምንም የምንኖረው በጦርነት ውስጥ ነው፡፡ በጦርነት ውስጥ እንደሆንን እናውቃለን? በጦርነት ውስጥ መኖር ባንወድም የምንኖረው በጦርነት ውስጥ ነው - በመንፈሳዊው ጦርነት፡፡
- በጦርነቱም ብዙ ሰዎችን አጥተናል፤ ምክንያቱም ጠላታችን በመካከላችን ነውና፡፡ በምንበርበት አውሮፕላን፣ በመኝታ ክፍላችን፣ በሥራ ገበታችን፣ በማኅበራዊ ሕይወታችን፣ መንፈሳዊ ተግባራትን ለማከናወን ስንነሳ ከጎናችን ሆኖ ስለሚዋጋን ውጊያው ብርቱ ነው፡፡ በሥጋ ጦርነት የጠላት ምሽግ፣ መንደር፣… ይታወቃል፡፡ ይሽኛው ተዋጊ ጠላት ግን መንፈስ ነው የሚገኘውም በመካከላችን ነው፡፡
- የዛሬው ትምህርት ዓላማ ምዕመናንን ማስፈራራት አይደለም፡፡
- ነገር ግን የሚያገሳ አንበሳ እንደሚጠብቀን ማሳወቅ ነው:: ‹‹ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና ›› ***<u>ቀዳ ጴጥ 5፡8፡፡</u>*** እንዳለ፡፡ ለዚህ ነው ሰዎችን ለመግደል የሚጨክኑ ሰዎችና …. ሌሎችም ድርጊቶች ዓለምን የክፋት መንደር ያደረጓት፡፡ ‹‹የማደርገውን አላውቀውምና አላውቅምና የምጠላውንም ያን አደርገዋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውምና፡፡›› ***<u>ሮሜ 7፡15፡፡</u>*** ያለን ለዚሁ ነው፡፡
- አዎ በጦርነት ውስጥ ነን፤ ነገር ግን ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው፡፡ ጦርነቱ በእግዚአብሔርና በዲያቢሎስ መካከል የሚደረግ ነው፤ ዲያቢሎስ እግዚአብሔርንና የርሱ የሆነውን ይጠላልና፡፡

# መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፬

- መንፈሳዊ ውጊያዎች የድል አክሊልን የምንቀዳጅባቸው ስለሆኑ ስለራሳችን ጥቅም ሲል እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲያልፉ ይፈቅዳል፡፡
- እነዚህ ውጊያዎች ነጻ ፈቃዳችንን እንዴት እንደምንጠቀምበት ለመፈተንና በውጊያው ድል ካደረግንም ሰማያዊውን ሽልማት እንድንቀዳጅ ሲል በሕይወታችን ያሳልፋቸዋል፡፡
- ***ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት መቀናቀንና የሚሿትንም ሁሉ መዋጋት መታወቂያው ነው፡፡***
- እግዚአብሔርን በልጆቹ በኩል እየተዋጋ በጻድቁ ኢዮብ እንዳደረገው ይከሳቸዋል፡፡ ***ኢዮ 1 እና 2፡፡*** የቅድስናን ሕይወት በሚመሩትም ላይ ይቀናባቸዋል፤ ራሱ ያጣውን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ በረከት እንዳያገኙም ይጣጣራል፡፡
- ***የዲያቢሎስ ሁሉንም ሰው ስለሚዋጋ ከውጊያው የሚያመልጥ ሰው የለም፡፡***
- ስለውጊያው ስንናገር ውጊያው በዲያቢሎስ የሚቀሰቀስ፣ በኃይሎቹና በደጋፊዎቹ የሚደረግ ውጊያ ማለታችን ነው፡፡
- ከአዳምና ከሔዋን ከልጃቸውም ከቃየን አንስቶ ዲያቢሎስ ሰዎችን ሲዋጋና በዘላለማዊ ሞት ፍርድ ሥር ሊጥላቸውም የተቻለውን ሁሉ ሲያደርግ ኖሯል፡፡
- ዲያቢሎስ ነቢያትን፣ ሐዋርያትንና እንደ ልበ አምላክ ዳዊት ያሉ በንስሐ የተመለሱ የእግዚአብሔር መንፈስ የነበረባቸውን ሰዎች ሁሉ ሲጋፋ ኖሯል፡፡ እግዚአብሔርን አልታዘዝ በማለቱ የእግዚአብሔር መንፈስ ተለይቶት ‹‹ የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ፥ ክፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አሠቃየው።›› ***1ኛ ሳሙ 16፡14፡፡*** የተባለለት ሳዖልንም አሰቃይቶታል፡፡
- ስለዚህም የዲያቢሎስ ውጊያ ጀማሪ (ወጣንያን) ክርስቲያኖችን ወይም ኃጢአተኞችን ብቻ የሚፈትን አድርገን እንዳንቆጥር ይገባናል፡፡

# መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፭

- ***ዲያቢሎስ በመንፈሳዊ ሀብታት (ጸጋ) የሚያድጉትን ሳይቀር አብዝቶ ይዋጋልና ሁሉም ከመጠንቀቅ በቀር ከውጊያዎቹ ሁሉ በላይ አድርጎ ራሱን አይቁጠር፡፡*** ልበ አምላክ ዳዊት የእግዚአብሔር መንፈስ ከርሱ ጋር ቢሆንም በእግዚአብሔር ለንጉሥነት ቢቀባም በዝሙት ኃጢአት እንዴት እንደተፈተነና እንደወደቀ ዲያቢሎስም ውድቀቱን እንደተፈላለገ እናስተውል፡፡
- **ቅዱስ ጴጥሮስም ስለዲያቢሎስ** ‹‹ በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ ›› ***<u>ቀዳ ጴጥ 5፡8</u>*** **በማለት የጻፈልን በዲያቢሎስ ወጥመድ እንዳንያዝ በንቃት እንድንኖር፣ ለማሳሰብ ነው፡፡**
- **በኢዮብ *ታሪክ* እግዚአብሔር ዲያቢሎስን ከወዴት መጣህ? ብሎ ሲጠይቀው** ‹‹ ሰይጣንም። በምድር ላይ ዞርሁ፥ በእርስዋም ተመላለስሁ ብሎ ለእግዚአብሔር መለሰ። ›› ***<u>ኢዮ 1፡7፣2፡2</u>*** **በማለት በሐዘን ሆኖ መልሶለታል፡፡ በርግጥም የመመላለሱ ዋና ዓላማ የሚጥልበትን ወጥመድ በማኖር ሰዎችን ለመጣል ነበር፡፡**
- ***ዲያቢሎስ የሚዋጋው ሰው ምንም ያህል ብርቱ ቢሆን ተስፋ ሳይቆርጥ ይዋጋል፡፡*** **ስለ ኃጢአትም** ‹‹ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና እርስዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው። ›› ***<u>ምሳ 7፡26</u>*** **ተብለናል፡፡**
- **ዲያቢሎስ አሥራሁለቱን የጌታችንን ደቀመዛሙርት ለመዋጋት አላመነታም፡፡ ጌታችንም ለቅዱስ ጴጥሮስ** ‹‹ ጌታም፦ ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።›› ***<u>ሉቃ 22፡31-32</u>*** **በማለት ነግሮታል፡፡**
- **እግዚአብሔር በሰረጋላው ወደ ሰማይ ስለ ወሰደው ነቢዩ ኤልያስም ቅዱስ ያዕቆብ** ‹‹ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ ›› ***<u>ያዕ 5፡17</u>*** **በማለት የገጠመውን በማስታወስ ጽፎልናል፡፡**
- **ዲያቢሎስ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በገዳመ ቆሮንቶስ ሦስት ፈተናዎችን በማቅረብ ፈትኖታል፤ በጾመ ጊዜም ዐርባ ቀን ፈትኖታል፡፡** ***<u>ማቴ 3፡13-17፣ ማቴ 4፣ ማር 1፡13፣ ሉቃ 4፡2፡፡</u>***

# መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፩

- ስለ ጌታችንም ‹‹እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና። ›› ***ዕብ 2:18*** የተጻፈልን በፈተናችን ሁሉ መጽናኛ ይሆነን ዘንድ ነው፡፡ ስንፈተን ልንጨነቅ አይገባንም ጌታችንም ተፈትኗልና፤ ተፈትኖም ፈተናውን ድል እንዳደረገ ድል የምናደርግበትን ኃይል ይሰጠናል፡፡
- ***የዲያቢሎስ ውጊያ በእግዚአብሔር፣ በመንግሥቱና የተቀደሰን ቤተ መቅደሶቹ በሆን በኛ ላይ የተከፈተ ውጊያ ነው፡፡***
- ዲያቢሎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ መቀናቀን የሚፈልግ ሲሆን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመጋፋት ‹‹የተመረጡትንም በማሳት›› ***ማቴ 24:24***። ሲሳካለት ደስ ይሰኛል፡፡
- ‹‹ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ›› ***ሉቃ 15:10*** እንደሚሆን ያለጥርጥር ዲያቢሎስ አንድ ጻድቅ ሰው ሲወድቅና ያንም ሰው የሌሎች ማስፈራሪያ አድርጎ ሲያቀርበው ደስታ ያደርጋል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መንፈሳዊ ውጊያ ሲያብራራልን ‹‹የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።›› ***ኤፌ 6:11-12፡፡*** ብሎናል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መንፈሳዊ ውጊያ ለመቋቋም መንፈሳዊ የጦር ዕቃ ልብስ መልበስ እንደሚያስፈልግ ‹‹ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም፡፡›› ***ዮሐ 15:5፡፡*** እንደነገረን የእግዚአብሔር እርዳታ አስፈልጎአቸዋልና ያስፈልገናል፡፡
- በነዚህ መንፈሳዊ ውጊያዎች የልበ አምላክ ዳዊትን ቃላት ማሰብ ምንኛ መልካም ነው፡፡ ‹‹ ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና እናንተንም በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል።›› ***ቀዳ ሳሙ 17:47፡፡***
- ***መንፈሳዊ ውጊያዎች የሚለያዩ ይሁኑ እንጂ የማያቋርጡና ፈጽመው የማያልቁ ናቸው፡፡***

# መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፬

- በሥጋ እስካለን ድረስ እስከሞት ድረስ የሚቀጥል መንፈሳዊ ውጊያ ይኖራል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ።›› ***ቀዳ ጴጥ 1፡17፡፡*** በማለት ዲያቢሎስን በመፍራት ሳይሆን ወደ ጥንቃቄና ማስተዋል በምታደርስ ፍርሐት እንድንሆን ነግሮናል፡፡
- የዲያቢሎስ ውጊያው ለእያንዳንዱ ሰው እስከ ሞት ድረስ የሚቀጥል ሲሆን በዓለም ውስጥ ግን ዓለሙ እስኪፈጸም ድረስ ይዘልቃል፡፡ ዲያቢሎስ ከእስሩ በሚፈታበት ጊዜም ሳይቀር ‹‹ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፥ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን፥ እንዲያስታ ቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው።›› ***ራዕ 20፡7-8፡፡*** ዓለምን ያስታል፤ ‹‹ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ። ›› ***ካል ጢሞ 3፡1፡፡*** እንዳለ ዓለምን ያስጨንቃል፤ ‹‹ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ፡፡›› ***ቀዳ ጢሞ 4፡1፡፡***
- ጌታችን ዳግም ለፍርድ ከመምጣቱ በፊት ክህደትና የዓመፅ ሰው ይመጣሉ፤ ዲያቢሎስ የሚቻለውን ሁሉ አድርጎ ‹‹ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና›› ***ራእ 12፡12፡፡*** እንደተባለ ወደ ምድር ይወርዳል፡፡
- ***ይህ የዲያቢሎስ ውጊያ በተቀደሱ ወራቶች (በአጽዋማት) እጅግ ከፍ ያለ ይሆናል፡፡***
- ዲያቢሎስ ማንኛውንም መንፈሳዊ ሥራ ስንጀምር በመናደድ ኃይሉን ሁሉ በመጠቀም የማደናቀፊያ ወጥመዱን ሁሉ ያዘጋጅልናል፡፡ እንግዲህ መንፈሳዊ ሥራ ስንጀምር ውጊያውን፣ መሣሪያዎቹንና፣ ማደናቀፊያዎቹን ሁሉ ይጠቀማል፡፡
- እኛ መንፈሳዊ ሥራ ስንጀምር እርሱም ተቃውሞውን ይጀምራል፡፡
- እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የመሠረትን ከሆን ዲያቢሎስ ፈጽሞ አይደሰትም፤ መንግሥቱን አደጋ ውስጥ እንደምንጨምር ያውቃልና፡፡ አባቶች ከተናገሯቸው የጥበብ ቃላት ***‹‹በሌሊት ለሰዓታት ጸሎት የሚደወለው ደወል ካህናት ብቻ ሳይሆኑ ዲያቢሎስም ካህናቱን ለመዋጋትና እንዳይጸልዩ ለማድረግ ይነቃል፡፡››*** የሚለው ይህንን የበለጠ ግልጽ ያደርግልናል፡፡

# <u>መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፩</u>

- እኛ ለጸሎት፣ ለዝማሬ፣ መንፈሳውያን መጻሕፍትን ለማንበብ፣ ትርጓሜያቸውንም ለማጥናት ለስግደትም ስንዘጋጅ ሰይጣን እኛን የሚዋጋበትን ጦርነት አዘጋጅቶ ይጠብቀናል እንኳ ዝም ብሎ አይተወንምና የተቀደሰውን ጸሎት ስናደርስ ለሚያሰናክሉን ነገሮች ሁሉ ልንዘጋጅ ይገባል፡፡ ***‹‹ልጄ ሆይ እግዚአብሔርን ለማገልገል ስትነሳ ለፈተናዎች ሁሉ ተዘጋጅ፡፡›› <u>መጽ ሲራ 2፡1፡፡</u>*** የሚለው የጥበብ ቃል ይህን የሚያሳስበን ነው፡፡
- ዲያቢሎስ ሊቋቋሙት የሚዘጋጁትን ሁሉም የበለጠ ለመዋጋት ይነሳልና ‹‹ ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።›› ***<u>ቀዳ ቆሮ 15፡58፡፡</u>*** እንደተባልነው ወደ ኋላ እንዳንመለስ በርትተን እንገኝ፡፡
- ***እኛ ለትግል ስንዘጋጅ እርሱ ለውጊያ፣ እኛ መንፈሳዊ ነገሮችን ስንጀምር እርሱ ተቃውሞውን ማደናቀፊያውን ያዘጋጃል፡፡***
- ለምሳሌ እኛ መጾም ስንጀምር ይናደዳል፤ በመጾማችን ‹‹የተጣልን እንዳንሆን ሥጋችንን እንጎስምበታለን፡፡›› ***<u>ቀዳ ቆሮ 9፡27፡፡</u>*** ነፍሳችንም ተነስታ እግዚአብሔርን ታገኛለችና ዲያቢሎስ ይህንን አይፈልግም፡፡
- ይልቁኑ በዐቢይ ጾም ታላቅ ዝግጅት አድርገን ስንጾም ጌታችን ጾሞ እርሱን ድል ያደረገበትን ያስታውሰዋልና ***<u>ማቴ 4</u>*** በዚህ የጾም ወቅት ችግሮችን በማስነሳት ሰዎች በነዚያ ችግሮችና ጉዳዮች ተጠምደው መንፈሳዊውን ነገር እንዲረሱት ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ከነዚህ የቤተ ክርስቲያን አጽዋማት ችግሮችና ፈተናዎች እንደሚኖሩ አንዘንጋ፡፡
- ***ያለምንም ጥርጥር መንፈሳዊ ተግባራት ዲያቢሎስን ምቾት ያሳጡታል፡፡***
- ዲያቢሎስ እርሱ አጥቶታልና ከእግዚአብሔር ጋር ግኑኙነት ያለው መንፈሳዊ ሰው ሰላም ይነሳዋል፡፡ ምክንያቱም እርሱ መንፈስ ሆኖ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ስላደፈና ***<u>ማቴ 12፡45፣ ማር 1፡27፡፡</u>*** ሰው ግን ምንም ሥጋ ለባሽ ቢሆን በመንፈሳዊነቱ ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር ከፍ ትላለችና ዲያቢሎስ ምቾት ያጣል፡፡

# መንፈሳዊ ውጊያዎች - ፩

- በመጀመሪያ ዲያቢሎስ በአዳምና በሔዋን በመቅናት በኃጢአት እንዲወድቁ በማድረግ ሞትን አምጥቶባቸዋል፡፡
- ***ዲያቢሎስ የሚቀናው ምቀትም የሚያጣው በመንፈሳዊ ተግባራቸው ስኬታማ በሆኑ ሰዎች ነው፡፡***
- ዲያቢሎስ ወደ እግዚአብሔር በቀረቡ እግዚአብሔርም በሚረዳቸው ሰዎች ይቀናል ምቀትንም ያጣል፤ ንስሐ በሚገቡት ስለ ንስሐቸው፣ በአምልኮተ እግዚአብሔር ስለሚኖሩት ስለ ትጋታቸው፣ ልበ ትሑታንን ስለትሕትናቸው፣ ልበ ንጹሐን ለሆኑት ስለ ንጽሕናቸው ይቀናባቸዋል ምቀትንም ያጣል፡፡
- ታዲያ በርሱና በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ያሉትን በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ቸልተኞች የሆኑትን ስለምን ይዋጋቸዋል? በሁኔታቸው ስለሚደሰት፣ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግና፣ ወደ ሚከፋ ሁኔታ ውስጥ ለመጨመር ሲል ይዋጋቸዋል፡፡
- ***ስለ ዲያቢሎስ ውጊያ ስናነሳ ሰዎች የሚፈተኑባቸው ሦስት ዋና ዋና የመንፈሳዊ ውጊያ ዓይነቶችን አሉ፡፡ እነርሱም፡-***
  - ዲያቢሎስ በቀላሉ ወይም በኃይል የሚፈትነውን ሰው አለ፡፡
  - ዲያቢሎስ መጀመሪያ ቢያስጀምረውም በራሱ ፈቃድ፣ ድካምና መጥፎ ልምድ ተታልሎ የሚፈተን  ሰው፡፡ እንዲህ ያለው አንዳንዱ ሰው በሥጋው፣ ሌላው በጋዛ ሐሳቡ የሚፈተንም ሰው አለ፡፡
  - በሐሰተኛ (ሰዎች) ምስክሮች፣ በኃጢአተኞች ወይም ‹‹የሰይጣን ደጋፊ ማኅበርተኞች ወይም የዲያቢሎስ ኃይሎች›› በምንላቸው ክፋት በሚደረግበት አካባቢ የሚፈተን ሰውም አለ፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org